በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል::

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ጁጁ□ል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተ□ጁ□□ ቀርበ□ል::

- □□ቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፤</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ለዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን መቀጣታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ አንድ ዕቃ አቅራቢ በውሉ ከተቀመጠው ጊዜ ገደብ በላይ 77 ቀናት አዘግይቶ በማቅረቡ መቀጣት የነበረበትን የጉዳት ካሳ ብር 71,973.44 እንዲከፍል ያልተደረገ መሆኑ፣
2. ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 4,919,347.57 የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣

3. ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት ዋናው ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው፤ ለፎቶ ኮፒና ፕሪንተር ግዥ ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 778,573.00 የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፤

4. የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመርያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች፤ ንዑስ አንቀጽ 3 ማንኛውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ዕቃው ወደ መስሪያ ቤቱ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ለግንባታ ሥራ አገልግሎት እንዲውሉ ሁለት ተሽከርካሪዎች (ቶዮታ ፒክአፕ) በብር 7,383,772.80 የተገዙ ሲሆን በዕቃ ገቢ ደረሰኝ (የሞዴል 19) ገቢ ያልተደረጉ መሆኑና ኮድ 4 የሰሌዳ ቁጥር ሊሰጣቸው ሲገባ ኮድ 3 አ.አ የተሰጣቸው መሆኑ፤

5. የግቢ ማስዋብ ሥራ ላከናወኑ የቀን ሰራተኞች ብር 224,150.00 እና በግቢው ውስጥ የሸክላ ንጣፍ ሥራ ለሰሩ የቀን ሰራተኞች ብር 126,000.00 በድምሩ ብር 350,150.00 ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን የሰራተኞቹ የሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ (Attendance Sheet) ከክፍያ ሰነዱ ጋር ተያይዞ ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

6. የዩኒቨርሲቲው የግዥ ክፍል የመንግስትን ወጪ ሊቀንስ በሚችል መልኩ የግዥ ፍላጎትን ከየክፍሉ በማሰባሰብ ግልፅ ጨረታ አውጥቶ በርካታ ድርጅቶችን በማሳተፍ የመንግስት ጥቅም ማስጠበቅ ሲገባ፣
   - ያለውድድር የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በብር 8,871,650.02 በቀጥታ ግዢ የተፈጸመ መሆኑ፤
   - ግዥዉ በዕቅድ ተይዞ በግልፅ ጨረታ በጥቅል መግዛት ሲገባው በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ በብር 4,092,749.75 የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ የተፈጸመ መሆኑ፤

7. ለሰማኒያ ስምንት (88) ሰራተኞች በተለያዩ ቀናት በተለያየ የክፍያ ተመን የሂዱበት ቦታና በመስክ ሥራ የቆዩበት ቀናት ሳይገለጽ በድምሩ ብር 175,662.00 የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

8. የተማሪዎች ምግብ አቅርቦት ግዢ ኦዲት ሲደረግ ለጤፍ ግዢ ብር 6,960.00 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤

9. የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ የተመዘገበ ብር 585,772.88 የወጪ ሂሣብ የተገኘ መሆኑ፤
10. በቅድሚያ የተከፈለ ብር 3,008,537.75 በተሰብሳቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤
11. በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ብር 38,413,381.02 ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤
12. በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተከፈለ) ብር 268,334.52 ተከፋይ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡

ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤

ምንም እንኳን በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖራቸውም መሠረታዊና ጉልህ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥርና የአፈጻጸም ድክመቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡

1. ለዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለት በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት፤ ከካፒታል በጀትና እና ከውስጥ ገቢ ብር በድምሩ ብር 36,001,013.00 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች፤

1. የዩኒቨርሲቲው የንብረት አጠባበቅና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፤
   - መወገድ የሚገባቸው 346 ትናንሽ አሮጌ ጎማዎች፤ 60 ትላልቅ አሮጌ ጎማዎች፤ 25 ኋይት ቦርድ፤ 31 OK ፕሪንተር፤ 3 ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ 160 ኮምፒዩተር ፤ 65 የኮምፒዩተር እስከሪን፤ 3 የውሃ ማጣሪያዎች፤ 2 ፕሮጀክተሮች፤ 100 እስታብላይዘሮች፤ 40 የመኪና ባትሪዎች፤ 20 ትልቅና ትንሽ የብረት ቁም ሳጥኖች፤ ሳይወገዱ በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኑ መሆኑ፤
   - 4 የዲሽ ሳህኖች፤ በርካታ የተማሪ ወንበሮች እና 580 የቤት ክዳን ቆርቆሮዎች መወገድ ሲገባቸው በዋናው ግቢ ሜዳ ላይ ተጥለው የሚገኝ መሆኑ፤
2. የዩኒቨርሲቲው የተሽከርካሪዎች አጠባበቅና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፤
   - ኮድ ኢት 4-12236 ላንድ ኩሩዘር በብልሽት ምክንያት ከ7 ወር በላይ የቆመ መሆኑ፤

- ኮድ ኢ.ት 4-12470 ማርቸዲስ በብልሽት ምክንያት 5 ዓመት የቆመ መሆኑ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-14961 ታታ በብልሽት ምክንያት ከ1 ዓመት በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-12315 ሚትስቡሺ ለረጅም ዓመታት በብልሽት ምክንያት የቆመ መሆኑ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-14962 ታታ በብልሽት ምክንያት ከ9 ወር በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-17441 ማዝዳ ፒክአፕ በግጭት ምክንያት ከ2 ወር በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-20774 ሚኒባስ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌለው መሆኑ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-12998 እና ኢ.ት 4-14195 ኒሳን ፒክአፕ መኪናዎች የኪሎ ሜትር ቆጣሪ (ጌጃቸው) የማይሰራ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡ የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት

ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>**የገቢ ሂሣብ፤**</u>

1.1.1 <u>**ግኝት፤ ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣ፤**</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3ሸ እና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 27/4ሀ መሰረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ስራውን አጠናቆ ባያስረክብ ላዘገየው ጊዜ የውሉ መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛውን መቀጣት እንዳለበት ያመለክታል፡፡ በዚሁ መሠረት የዕቃ አቅራቢዎች በተገባው ውል መሠረት ማቅረባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ከሊፎ የጠቅላላ ንግድ ድርጅት የተለያዩ የICT ዕቃዎችን ለማቅረብ በቀን 04/06/09 ከዩኒቨርሲቲዉ ጋር ዉል የፈጸመ ሲሆን በዉሉ መሰረት አጠናቅቆ ዕቃዉን ማስረከብ የነበረበት በ20 ቀናት ገደብ ሲሆን ከተሰጠዉ የጊዜ ገደብ 77 ቀናት አሳልፎ በቀን 12/09/2009 በዕቃ ገቢ ደረሰኝ ቁጥር 668729 ላቀረባቸዉ ዕቃዎች በመመሪያውና በውሉ መሰረት መቀጣት የነበረበትን የጉዳት ካሳ (934,720.00x77ቀናትx1/1000) ብር 71,973.44 እንዲከፍል ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

1.1.2 <u>***ሥጋት፤***</u>

- አስፈላጊነታቸው በመንግስት ታምኖባቸው የወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎችን መተላለፍ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በመመሪያው መሰረት የጉዳት ካሳ እንዲከፍል አለማድረግ መንግስት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

1.1.3 <u>**የማሻሻያ ሀሳብ፤**</u>

ዩኒቨርሲቲው ኃላፊነታቸውን በማይወጡ የዕቃ አቅራቢዎች ላይ የሚፈለገውን የጉዳት ካሳ (ቅጣት) በውሉ መሠረት ሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ ማድረግ

ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ዕቃዎች በወቅቱ እንዲቀርቡ የስራ አመራሩ ተገቢውን ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

በቀጣይ የጉዳት ካሳ ክፍያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ሁኔታ ከአቅራቢው ድርጅት ጋር በመነጋገር ተግባራዊ የምናደርግ ይሆናል፡፡

2. **የወጪ ሂሳብ፤**

2.1.1 **ግኝት፤ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ክፍያዎች፤**

የፌደራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 7 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች ስር ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት ኦሪጅናል ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 4,919,347.57 የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ በሰንጠረዡ ተመልክቷል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የባ/ወ/ማ/ ቁጥር	የክፍያው ምክንያት	አቅራቢው ድርጅት	የገንዘቡ ልክ
1	19/01/09	0867457	ለህትመት አገልግሎት	ምዕራፍ ፕሪንተርስ	158,642.50
2	25/05/09	960810	ለተማሪዎች ዶርሚቶሪ ግንባታ 5ኛ ክፍያ	ኬሚያ ጠቅላላ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ	2,436,065.07
3	09/02/09	0867499	ለጤፍ ግዥ	ኦሮሚያ ግብርና ፌዴሬሽን	232,000.00
4	01/03/09	933014	ለጤፍ ግዥ	ኦሮሚያ ግብርና ፌዴሬሽን	2,092,640.00
				ድምር	**4,919,347.57**

2.1.2 **ሥጋት፤**

የተሟላ የክፍያ ማስረጃ ሳይቀርብ የወጪ ሂሣብ ተወራርዶ የሚመዘገብ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ሊባክን ይችላል፡፡

2.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ለክፍያው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

2.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

ከድርጅቶቹ ጋር በመነጋገር ተፈላጊውን የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እንዲሟላ በማድረግ ለቀረበው ግኝት የማስተካከያ እርምጃ የምንወስድ ይሆናል፡፡

2.2.1 <u>ግኝት፤ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ ክፍያ፤</u>

በፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተመለከተው የመንግስት መ/ቤቶች ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጭዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት ለግዥ ክፍያዎች ተገቢው ደረሰኝ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 13/01/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0839997 ለፎቶ ኮፒና ፕሪንተር ግዥ ለናኖዳስ ትሬዲንግ ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 778,573.00 የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.2.2 <u>ሥጋት፤</u>

በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የወጪ ሂሳብ እንዲመዘገብ ማድረግ የገንዘብ ክፍያ ደረሰኝ ሲቀርብ ሂሣቡ በድጋሚ በወጪ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

2.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በዱቤ ሽያጭ ለተመዘገበው የወጪ ሂሳብ የገንዘብ ክፍያ ደረሰኝ እንዲቀርብ እንዲደረግና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡

2.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በአሁኑ ወቅት ከድርጅቱ ጋር ውይይት በማድረግ ህጋዊ የክፍያ ደረሰኝ እንዲያቀርብ ጥረት በማድረግ ላይ በመሆናችን በዚሁ አግባብ የሚስተካከል ይሆናል፡፡

2.3.1 <u>ግኝት፤ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ያልተዘጋጀለት የተሽከርካሪ ግዢ፤</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ ከሚገቡ ጥንቃቄዎች ውስጥ አንዱ ዕቃ ወደ መ/ቤቱ ዕቃ

መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞደል19) መቅረቡን ማረጋገጥ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለግንባታ ሥራ አገልግሎት እንዲውሉ ሁለት ተሽከርካሪዎች (ቶዮታ ፒክአፕ) በቀን 24/08/2009 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 932950 በብር 7,383,772.80 የተገዙ ሲሆን በዕቃ ገቢ ደረሰኝ (የሞዴል 19) ገቢ ያልተደረጉ መሆኑና ኮድ 4 የሰሌዳ ቁጥር ሊሰጣቸው ሲገባ ኮድ 3 አ.አ የተሰጣቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

2.3.2 ***ሥጋት፤***

ለዕቃዎች ግዢ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያው የሚወራረድ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ሊባክን ይችላል፡፡

2.3.3 ***የማሻሻያ ሀሳብ፤***

ለተሽከርካሪዎቹ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ እንዲዘጋጅላቸውና ኮድ 4 የሰሌዳ ቁጥር እንዲሰጣቸው ማድረግ ይገባል፡፡

2.3.4 ***የሥራ አመራሩ ምላሽ፤***

ከዩኒቨርሲቲው የእስታዲየም ግንባታ ስራ ጋር በተያያዘ ለአማካሪ ድርጅት የትራንስፖርት አገልግሎት ለማቅረብ ይቻል ዘንድ በግንባታ ውሉ ዝርዝር ውስጥ የተሽከርካሪ፣ ፕሮጀክቱ እስከምጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የነዳጅ እና መሰል የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥ ወጪዎች የተካተተ በመሆኑ ግዥው በዚህ አግባብ የተከናወነ ሲሆን፤ የተሽከርካሪዎች ኮድ ከ 3-አ.አ ወደ ኮድ 4-ኢ.ት ለውጥ አድርጎ መጠቀም ከግንባታው ስራ ጋር ከቦታ ወደ ቦታ የሚደረገውን እንቅስቃሴ የሚገድብ ከመሆኑ ባሻገር ፕሮጀክቱ በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዲፈጸም የበኩሉን አሉታዊ አስተዋፆኦ የሚያደርግ በመሆኑ፤ የተሰጠውን አስተያየት በግብአትነት በመወሰድ ከፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የኦዲት ማስታወሻ ተግባራዊ የማስተካከያ እርምጃ የምንወስድ ይሆናል፡፡

2.4.1 ***ግኝት፤ የሰዓት መቆጣጠሪያ ያልቀረበለት የቀን ሰራተኞች ክፍያ፤***

በፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተመለከተው የመንግስት መ/ቤቶች ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጭዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 25/12/08 በCPV ቁጥር 0129903 የግቢ ማስዋብ ሥራ ላከናወኑ የቀን ሰራተኞች ብር 224,150.00 እና በቀን 30/02/09 በJVቁጥር 104584 በግቢው ውስጥ የሽክላ ንጣፍ ሥራ ለሰሩ የቀን ሰራተኞች ብር 126,000.00 በድምሩ ብር 350,150.00 ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን የሰራተኞቹ የሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ (Attendance Sheet) ከክፍያ ሰነዱ ጋር ተያይዞ ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋጋጥ አልተቻለም፡፡

2.4.2 ***ሥጋት፤***

የሰዓት መቆጣጠሪያ ማስረጃ ሳይቀርብ ለቀን ሠራተኞች ክፍያ የሚፈጸም ከሆነ ላልተሰራ ሥራ ክፍያ ሊፈጸም ይችላል፡፡

2.4.3 ***የማሻሻያ ሀሳብ፤***

የቀን ሰራተኞች ክፍያ በተገቢው የሰዓት መቆጣጠሪያ ማስረጃ መደገፍ ይኖርበታል፡፡

2.4.4 ***የሥራ አመራሩ ምላሽ፤***

ቀደም ሲል ወጥነት ባልነበረው ሁኔታ በስራ ላይ የተገኙትን /ያሉትን ሰራተኞች ለማመልከት ሲባል የ✓ ወይም × ምልክት አልፎ አልፎ የመጠቀም ሁኔታ የነበረ ሲሆን፤ ነገር ግን በኦዲት ማስታወሻው የተሰጠውን አስተያየት በአኮቴ በመቀበል ከውይይቱ ማግስት ጀምሮ ማንኛውም የሰአት ፊርማ መቆጣጠሪያ በግለሰቦቹ ፊርማ ወይም በእጅ አሻራ እንዲረጋገጥ ብቻ በማድረግ ለቀረበው ግኝት የማስተካከያ እርምጃ የወሰድን ሲሆን በቀጣይ ቀደም ሲል ይቀርብ በነበረው አስተያየት ሁናቴ እንኳን በስተት ቢቀርብ ተገቢ የሆነ አስተያየት በመስጠት ታርሞ እንዲቀርብ በማድረግ ቀጣይነት ባለው መልኩ በፊርማ ወይም በእጅ አሻራ ብቻ ተረጋግጦ እንዲቀርብ በማድረግ የምንሰራ መሆኑን ግንዛቤ እንዲያዝበት እንጠይቃለን፡

2.5.1 ***ግኝት፤ ያለውድድር በቀጥታ የተፈጸመ ግዢ፤***

የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 55 ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ አንቀፅ 55.4 የመንግስት መ/ቤቱ ለሚጠቀምበት ዕቃ የሚያስፈልገው መለዋወጫ የሚገኘው ቀደም ሲል ዕቃውን ከሸጠው አቅራቢ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ሆኖም ለዚህ ንዑስ አንቀፅ አፈፃፀም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ሀ/ የመንግስት መ/ቤቱ በቂ የገበያ ጥናት ማድረግ እና ሌላ የተሸለ አማራጭ ገበያ ላይ ከሌለ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ለ/የመንግስት መ/ቤቱ ለሚጠቀምበት ዕቃ ከሚገዛው

መለዋወጫ ብዛት፣ ተደጋጋሚነት እና የገንዘብ መጠን አንፃር ወደፊት ሌላ አማራጭ መፈለግ የሚያስፈልገው መሆኑንና አለመሆኑን መወሰን ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም አንቀፅ 55.6 ላይ ግዥው ከሌላ አቅራቢ እንደሚፈፀም ቢደረግ የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት መ/ቤቱ ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ጋር ተጣጥሞ የማይሄድ መሆኑ በባለሙያ ሲረጋገጥ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ በዚሁ መሰረት የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎት ግዢ ያለውድድር በቀጥታ በብር 8,871,650.02 ግዢ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የወ/ማ/ቁ	አቅራቢው ድርጅት	የክፍያው ምክንያት	የገንዘቡ ልክ
1	24/4/09	931085	ካፌ አላሂ ዶሬ	ለተደራራቢ አልጋ ግዥ፤	1,108,025.00
2	20/3/09	933347	አል-አሚን ሕንጻ መሳሪያ	ለተማሪዎች መኝታ ችፕውድ	1,159,200.00
3	08/2/09	087648	ማህ አጠቃላይ አስመጪ	ለሪዞ ማሽን ግዥ	1,840,000.00
4	03/2/09	086740	ካራማራ እስፖንጅ ፋብሪካ	ለፍራሽ ግዥ፤	1,543,932.50
5	28/3/09	931064	ሀብታሙ ታደሰ	ለፓወር ጀነሬተር ግዥ	1,965,034.90
6	29/6/09	961998	ዩኒቨርሳል የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካ	ለሌዘር ቦርሳ	220,210.00
7	15/7/09	931213	>> >>	ለሌዘር ቦርሳ	220,210.00
8	1/10/09	931354	አቡበከር ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ	ለፍሳሽ ውሃ ማስወገጃ ሥራ	336,629.29
9	29/7/09	931265	መውሊድ ኢስማኤል	ለአካባቢ ጥርጊያ ሥራ	478,408.33
				ድምር	8,871,650.02

2.5.2 ሥጋት

ግዥ በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ ከሆነ ኢፍትሐዊነትንና የገንዘብ ብክነትን ያስከትላል፡፡

2.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ

ግዥዎች በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

2.5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

የግዥ ህጉ እንደሚደነግገው ሁሉንም አቅራቢዎች በማሳታፍ በግልጽ ጨረታ አውጥቶ ግብአቶችን በአስቸኳይ ለተማሪዎች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ለማድረግ የሚወስደውን ተጨማሪ ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ብሎም ይህንኑ የጨረታ ሂደት ተጠቅመን አሸናፊ አቅራቢ ከመሀል የሀገሪቱ ክፍል ቢሆን አቅርቦቱ ሊኖረው ከሚችለው የትራንስፓርት መስተጓጎል እና መዘግየት ብሎም ለተጨማሪ የሀገር ሀብት ብክነት እና ጉዳት ለመዳረግ በር የሚከፍት በመሆኑ እና ወቅታዊ ምላሽ ከመስጠት አኳያ የተከናወነው የቀጥታ ግዥ ግድ ሊሆን የቻለ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.6.1 ግኝት፤ በዋጋ ማቅረቢያ የተፈጸመ ግዥ፤

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 33/2 እና ሰኔ 2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀጽ 15/2 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ በአዋጁ አንቀጽ 33/4 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ አዋጁ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ሥርዓቶችን ለመሸሽ በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን መከፋፈል እንደሌለባቸው እንዲሁም፣ በመመሪያው አንቀጽ 24/1 እና 24/4 መሠረት ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋቸው በመመሪያው በተጠቀሰው መሠረት በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ ለመፈፀም እንደሚቻል የተገለጸ ቢሆንም የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ግዥው በዕቅድ ተይዞ በግልፅ ጨረታ በጥቅል መገዛት ሲገባው በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ በብር 4,092,749.75 የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ተፈጽሟል፡፡ ዝርዝሩ በሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የBPV ቁጥር	አቅራቢው ድርጅት	የክፍያው ምክንያት	የገንዘቡ ልክ
1	26/04/09	931093	ሉል ኢንተርፕራይዝ	ለመጻፊያ ሰሌዳ	777,975.00
2	30/07/09	961966	>> >>	ለዋይትና ግሪን ቦርድ	422,395.00
3	19/05/09	960738	ከበድባድ የአከባቢ ጥበቃና ጽዳት	ለዛፍና አበባ ዘር	369,360.00
4	2/02/09	08674	ብርከሉል ኢንተርፐራይዝ	ለተማሪዎች ምግብ ቤት የሚዉሉ ዕቃዎች ግዥ	197,685.00
5	22/09/09	932893	ጉዳል ጠቅላላ ተቋራጭ	ለውሃ መውረጃ ቦይ ጥገና	461,518.00
6	06/06/09	931119	>> >>	›› ››	497,375.00
7	02/08/09	932904	Egan construction	ለላበራቶሪ ጥገና	497,950.00
8	22/06/09	931118	ከአል በዴ ጠቅላላ ተቋራጭ	ለካፍቴሪ መጸዳጃ ቤት	475,600.00
9	03/09/09	932814	ከከሊፎ ጠቅላላ ንግድ	ለኤሌክትሪክ ዕቃዎች	197,391.75
10	30/08/09	932947	ከአብዱ ሀሴን አስመጪ	ለኤሌክትሪክ ዕቃዎች	195,500.00
				ድምር	4,092,749.75

2.6.2 <u>ስጋት፤</u>

ግዥ በአዋጁና መመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባ፣ የአፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥም ይችላል፡፡

2.6.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ግዢዎች በግዢ መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2.6.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በወቅቱ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም ተያያዥ ደንብና መመሪያዎችን ዋቢ አድርጎ ግዥውን ለመፈጸም ተቋሙ ዝግጁ የነበረ ቢሆንም በወቅቱ ከነበረው ነባራዊ ሁኔታ አኳያ በዘርፉ ቁጥራቸው ውስን ጨረታ አውጥቶ ተጫራቾችን ለማስተናገድ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ካለመኖሩ ባሻገር ውስን የግዥ ዘዴን ተጠቅሞ ግዥውን ለማከናወን የሚያስችል በቂ የተጫራቾች ቁጥር ተሟልቶ ባለመገኘታቸው እና ተጨማሪ ግዜን በመውሰድ ግዥውን ለማከናወን መሻት የሚያከትለውን አሉታዊ ውጤት ግምት ውስጥ በማስገባት ይህንኑ የግዥ ዘዴ ተጠቅሞ በአስቸኳይ አቅርቦቱን እውን ማድረግ የውዴታ ግዴታ የሆነብን በመሆኑ ሳቢያ ከተማሪዎች ቅበላ ማግስት ጀምሮ ሰላማዊ ከባቢ በመፍጠር መማር ማስተማሩን ማስቀጠል ለነገ የማይባል ባለመሆኑ ምክንያት ከላይ የተመለከቱትን በአስገዳጅ ሁኔታ የተከናወኑትን የግዥ ዘዴዎችን ተጠቅሞ በወቅቱ ምላሽ መስጠት አቅርቦቶቹ ባለመሟላታቸው ሊፈጠር ከሚችለው የመማር ማስተማር ብሎም የዩኒቨርሲቲው ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ ከሂሳብ ሚዛን አኳያ ሲፈተሽ ፋይዳቸው በእጅጉ የላቀ በመሆኑ ግንዛቤ እንዲያዝባቸው እየጠየቅን በቀጣይ ከተፈጠረው አስገዳጅ ሁኔታ ውጭ ግዥዎችን በመንግስት የግዥ አዋጅ ደንብ፣ መመሪያዎች መሰረት ከዚህ ቀደም ስራ ላይ እንደምናውል ሁሉ በቀጣይም በዚሁ አግባብ ብቻ ተፈፃሚ የምናደርግ መሆኑን በድጋሚ እናሳውቃለን፡፡

2.7.1 ግኝት፤ የውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ ሳይሞላ የተወራረደ የውሎ አበል ክፍያ፤

በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የቀን ውሎ አበል መመሪያ (ሰኔ 2004 ዓ.ም) ክፍል ሁለት አንቀጽ 5.1 ማንኛዉም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታዉ ወደ ሆነ ሌላ ስራ ቦታ ለስራ ሄዶ እለቱን መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳና እራት በተመደበባቸዉ የክልል ከተሞች ዞኖች እና ወረዳዎች የውሎ አበል ተመን መሰረት መከፈል እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በ30/10/09 በCPV ቁጥር 0130095 በሂሳብ መደብ 6231 ለ88 (ሰማኒያ ስምንት) ሰራተኞች በተለያዩ ቀናት በተለያየ የክፍያ ተመን የሄዱበት ቦታና በመስክ ሥራ የቆዩበት ቀናት ሳይገለጽ በድምሩ ብር 175,662.00 የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2.7.2 ስጋት፤

ማንኛውም ክፍያ በመንግስት መመሪያ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

2.7.3 የማሻሻያ ሃሳብ፤

የተጠቀሰው ክፍያ አግባብነት ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና የውሎ አበል ክፍያ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

2.7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የውሎ አበል ክፍያ የተከናወነባቸውን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ ያልተሟሉትን የውሎ አበል ቅጾች በማሟላት የማስተካከያ እርምጃ የወሰድን ሲሆን፤ በቀጣይ መሰል የአሰራር ክፍተት እንደይስተዋል አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ የምንሰራ ይሆናል፡፡

2.8.1 ግኝት፤ ለተማሪዎች ምግብ አቅርቦት በብልጫ የተከፈለ፤

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ የመንግስት መ/ቤቶች የገንዘብ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በአንቀጽ 9 የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ ክፍያ

ከመፈጸሙ በፊት አስፈላጊ የሆነ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ይገልፃል:: የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 08/02/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0867499 ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት የሚውል ጤፍ ግዢ ለኦሮሚያ ግብርና ፌዴሬሽን ብር 232,000.00 የተከፈለ ሲሆን በቀን 21/02/09 በቁጥር FWHGQO/3871/09 ከኦሮሚያ ግብርና ፌዴሬሽን በተፃፈ ደብዳቤ 97 ኩንታል ጤፍ መቅረቡ የተገለጸ በመሆኑ ብር 225,040.00 (2,320.00x97) መከፈል ሲገባው የ100 ኩንታል ጤፍ ዋጋ (2,320.00x100) ብር 232,000.00 በመከፈሉ ብር 6,960.00 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.8.2 ሥጋት፤

ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በጥንቃቄ የማይፈጸሙ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ሊባክን ይችላል፡፡

2.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በአግባቡ እንዲፈጸሙ የሥራ አመራሩ ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.8.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ያሉትን ማስረጃዎች እና ተጨማሪ ደጋፊ ሰነዶች መሰረት በማድረግ አስፈላጊውን የማጣራት ስራ በመስራት በቀጣይ ለግኝቱ ምላሽ የምንሰጥ ይሆናል፡፡

2.9.1 ግኝት፤ የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ወጪ፤

የወጪ ሂሳቦች ነሃሴ 1999 በወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ (Chart of Accounts) መሠረት መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በቀን 22/06/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 961976 ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት ለሚውል ሥጋ ግዢ የተከፈለው ብር 391,436.88 በ6216 ሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው በ6231 ሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፤

- በቀን 13/10/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 932704 ለቤት ሙከራ ዕቃዎች ግዥ የተከፈለው ብር 194,336.00 በ6215 ሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው በ6244 ሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፤ በድምሩ ብር 585,772.88 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.9.2 ስጋት፤

ወጪዎች በትክክለኛው የሂሳብ መደባቸው የማይያዙ ከሆነ የበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታውን ካለማሳየቱም በተጨማሪ በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

2.9.3 የማሻሻያ ሃሳብ፤

ዩኒቨርሲቲው በጀት የሚመደብለት በየወጪ ሂሳብ ርዕሱ ተለይቶ ስለሆነ የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ክፍያ መፈፀሙ መመሪያን የጣሰ ከመሆኑም በላይ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ምክንያት ስለሚሆን ለወደፊቱ ሊስተካከል ይገባል፡፡

2.9.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በቀጣይ መሰል የአመዘጋገብ ስህተት እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄና ክትትል የምናደርግ ይሆናል፡፡

2.10.1 ግኝት፤ በወጪ የተመዘገበ ቅድመ ክፍያ፣

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተመለከተው የመንግስት መ/ቤቶች ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ዩኒቨርሲቲው የግቢ ውስጥ አረንጓዴና ውበት (greening & beautification) ሥራ ለማሰራት ከጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ ጋር የብር 1,843,605.00 ውል የተዋዋለ ሲሆን በቀን 18/07/2009 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 931219 የውሉን 30% ብር 553,081.50 እንዲሁም በቀን 25/08/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 931150 ቀሪውን የውሉን 70% ብር 1,290,523.50 በድምሩ

ብር 1,843,605.00 ወደ ኢንተርፕራይዙ የሂሳብ ቁጥር ገቢ የተደረገና ሥራው ስለመሰራቱ ማስረጃ ሳይቀርብ በተሰብሳቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባው በ6221 ሂሣብ መደብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

- የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ የመምህራን ገዋን ለመሥራት በተገባው ውል በቀን 23/09/09 የውሉን 50% ቅድሚያ ክፍያ በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 923770 የተከፈለው ብር 297,533.75 በተሰብሳቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

- የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ የመምህራን ካራቫት ለመሥራት በተገባው ውል የውሉን 50% ቅድሚያ ክፍያ በቀን 25/09/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 932773 የተከፈለው ብር 353,625.00 በተሰብሳቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

- ዩኒቨርሲቲው የደንብ ልብስ ለማሰራት ከሐዋ መሀመድ ጋር በገባው ውል በቀን 25/09/09 የውሉን 30% በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 932787 የተከፈለው ብር 513,774.00 በተሰብሳቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 3,008,537.75 በተሰብሳቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.10.2 ስጋት፤

ዩኒቨርሲቲው ላወጣው ወጪ እቃውን ወይም አገልግሎቱን ማግኘቱን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

2.10.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፤

የወጪ ሂሳብ በሚመዘግብበት ወቅት ለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም አላግባብ በወጪ ለተመዘገበው ሂሣብ ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግ ይገባል፡፡

2.10.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ምንም እንኳን በወቅቱ ስለ ቅድመ ክፍያው ከድርጅቶቹ የተሰጡትን የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች መሰረት በማድረግ ክፍያው በተሰብሳቢ ሂሳብ በመመዝገብ እና በቀጣይ ከአገልግሎቱ አቅርቦት በኃላ በወጪ መመዝገብ የሚገባ መሆኑ እሙን ቢሆንም፤ ነገር ግን ከስራው ክንዋኔ እና ከክፍያው ፍፃሜ በኃላ በተሰብሳቢም ሆነ በወጪ የሂሳብ መደቦች ላይ ምንም አይነት የሂሳብ መጠን ለውጥ ወይም ልዩነት የማያስከትል አለመሆኑን ግንዛቤ እንዲያዝበት እየጠየቅን ፤ግኝቱ በቀረበው ማብራሪያ ሊስተካከል የቻለ ሲሆን፤በቀጣይ በየሂደቱ ተገቢ የሂሳብ ምዝገባ እየተከናወነ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ አስፈላጊውን ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ መሰል የአሰራር ምዝገባ ክፍተት እንዳይስተዋል የምንሰራ ይሆናል፡፡

3. የተሰብሳቢ ሂሳብ፤

3.1.1. ግኝት፤

በፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ 5/2003 አንቀጽ 8/4 መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት የዩኒቨርሲቲው የተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ሂሣብ ውስጥ በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ብር 38,413,381.02 የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩም፤

- በ4201 ሂሳብ መደብ (ተንጠልጣይ ሂሣብ) ብር 15,001,299.18 መወራረድ ካለበት ጊዜ ከአንድ ዓመት በላይ ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፤
- በ4203 ሂሳብ መደብ (ለሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ) ብር 722,597.00 ከ2004 ጀምሮ እስከ አሁን ያልተወራረደ መሆኑ፤
- በ4210 ሂሳብ መደብ (ለሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች) ብር 284,128.27 በ2008 ዓ.ም እና ከዚያ በፊት የተሰጠና በወቅቱ ያልተወራረደ መሆኑ፤
- በ4211 ሂሳብ መደብ (ለግዢ ሰራተኞች የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ) ብር 1,381,960.28 ከአንድ ዓመት በላይ ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፤

- በ4253 ሂሳብ መደብ (ለዕቃ አቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ) ብር 21,023,396.29 ከአንድ ዓመት በላይ ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

3.1.2 ***ሥጋት፤***

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለው የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፤ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

3.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ተሰብሳቢ ሂሣቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራሩ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

3.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

- በሂሳብ መደብ የተመለከተው 4201 ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 15,001,299.18 በኦዲት ስራው የተሸፈነውን የበጀት ዓመቱ 2009 አካቶ ካለፉት ዓመታት ዞሮ የመጣውን በመደመር የተስተዋለ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሲሆን በተለያዩ መምህራን ለጥናት እና ምርምር ስራ የሚውል እና በሌሎች ሰራተኞች ስም ወጪ ሆኖ በተመሳሳይ ለተለያዩ ተግባራት መፈፀሚያ የሚውል ሲሆን በተለይ በመምህራን ስራውን የማከናወን ባህሪ አኳያ በወቅቱ ያልተወራረደ ሲሆን በያዝነው የበጀት ዓመት በርካታ የተሰብሳቢ ሂሳብ ወደ ስራ ክፍሉ ማስረጃ በማምጣት እየተወራረደ ይገኛል፡፡
- በሂሳብ መደብ 4203 ተመዝግቦ ከሚታየው በሂሳብ ሚዛን ውስጥ ብር 643,742.97 የምዝገባውን ትክክለኛነት በማጣራት የሚወራረድ ሲሆን ቀሪው ብር 78,854.03 ቀደም ሲል የደሞዝ ቅድመ ክፍያ ተፈፅሞ ግለሰቡ የወሰደወን ሂሳብ ገቢ ባለማድረጉ እና ዩኒቨርሲቲው ለቆ በመሄድ ምክንያት ጉዳዩ በህግ አግባብ ተይዞ የሚገኝ ነው፡፡
- በሂሳብ መደብ 4210 እና 4211 ተመዝግቦ የተመለከተው ካለፉት የበጀት ዓመት ዞሮ የመጣ ሲሆን ከፊሉ በያዝነው የበጀት ዓመት ተወራርዶ በመመዝገብ ላይ የሚገኝ ሲሆን በቀሪዎቹ ላይ ጥብቅ ክትትል በማድረግ እንዲያወራርዱ በማድረግ

የተስተዋለውን የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዲቀንስ ከፍተኛ ጥረት የምናደርግ ይሆናል፡፡

4. **የተከፋይ ሂሳብ፤**

4.1.1. **ግኝት፤**

የተከፋይ ሂሳብ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በሂሳብ መደብ 5005 (በሌሎች ከፐይሮል ተቀናሽ ተከፋይ) ብር 41,364.49 እና በሂሳብ መደብ 5006 (የቅድመ-ግብር ተከፋይ) ብር 226,970.03 በድምሩ ብር 268,334.52 ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል (ሳይወራረድ) ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

4.1.2 **ሥጋት፤**

በተካፋይነት የተያዙ ሂሳቦችን በወቅቱ ለተጠቃሚዎቹ አለመክፈል ገንዘቡ ከዕቅድ ውጪ ለሆኑ ስራዎች እንዲውል መንገድ ይከፍታል፡፡ እንዲሁም የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ካልተከፈለ (ካልተወራረደ) በሕግ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

4.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

በተቋሙ በዕዳ (በተከፋይነት) የተያዙ ሂሳቦች ለሚመለከታቸው ክፍሎች ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም የሥራ አመራሩ በተከፋይ ሂሳብ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

ሰኔ 30/2009 ዓ.ም የሂሳብ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፤ ይኸውም ሂሳብ መደብ 5005 የተመለከተው የገንዘብ መጠን ብር 41,364.49 በበጀት ዓመቱ ተቀናሽ ሆኖ ለውስጥ ገቢ ተከፋይ የሚሆን ሲሆን በተመሳሳይ በሂሳብ መደብ 5006 የተመለከተው የገንዘብ መጠን ብር 226,970.03 በበጀት ዓመቱ ከተፈፀሙ የአገልግሎት እና የዕቃዎች ግዥ ክፍያዎች ላይ ተቀናሽ ሆኖ ለኢ/ገ/ጉ/ባ/ የሚተላለፍ የዊዝሆልዲንግ ሂሳብ ነው፡፡ በቀጣይ አስፈላጊው ማጣራት በማድረግ የምናስተካክል ይሆናል፡፡

5. የበጀት አጠቃቀም፤

5.1.1. ግኝት፤

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀት እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር ከመደበኛ በጀት ብር 109,236,644.41፣ ከካፒታል በጀት ብር 62,287,842.22 እና ከውስጥ ገቢ ብር 280,115.81 በድምሩ ብር 171,804,602.44 ሳይሰራበት ተራፊ ሆኖ የተመለከተ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ ለሥራ ተቋራጮች በሂሳብ መደብ 4251 ብር 101,271,454.32 እና ለዕቃ አቅራቢዎች በሂሳብ መደብ 4253 ብር 34,532,135.12 በድምሩ 135,803,589.44 የቅድሚያ ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 36,001,013.00 ሳይሰራበት ተራፊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

5.1.2 ሥጋት፤

የተፈቀደው በጀት በዕቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ በሌሎች መ/ቤቶች ሊሰራበት የሚችለውን በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

5.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስ አዋጅ መሰረት በስራ ላይ እንዲያውል የተቋሙ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

5.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤ ስራ ላይ ያልዋለ በጀትን በተመለከተ እንደሚታወቀው በሂሳብ ምዝገባ መሰረት ለተለያዩ መምህራን፣ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ለምርምር እና ጥናት

እንዲሁም ለሌሎች ተግባራት የሚውል የቅድመ ክፍያ በሂሳብ መደብ 4201 የተፈፀሙ ፤በ4210 ለሌሎች የቅድመ ክፍያዎች እና በሂሳብ መደብ 4211 ለዕቃ ግዥ ተከፍይ የሆነው ሂሳብ ተመዝግበው የሚገኙት በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ በመሆኑ በወጪ ሪፖርት ውስጥ ባለመወራረዳቸው ምክንያት ተመዝግበው ተካተው የማይገኙ በመሆናቸው የወጪው ሂሳብ ሚዛኑን በተመለከተው የበጀት መጠን ዝቅ ብሎ እንዲታይ ከማድረጉ ባሻገር ከተጠቀሱት የበጀት አርዕስቶች ወጪ በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ በበጀት ዓመቱ ፍፃሜ በአንዳንድ የሂሳብ መደቦች ስራ ላይ ሙሉ በሙሉ ያልዋሉ በመሆናቸው የበጀት አጠቃቀሙ አፈጻፀም ዝቅ እንዲል የራሳቸውን ድርሻ አበርክተዋል ፡

6. <u>የንብረት አያያዝና አመዘጋገብን በተመለከተ፤</u>

6.1 <u>ግኝት፤</u>

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅ እና አመዘጋገብ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተገለፁት ሁኔታዎች እና ድንጋጌዎች መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

<u>**ቋሚ ዕቃዎችን በተመለከተ፤**</u>

- መወገድ የሚገባቸው 346 ትናንሽ አሮጌ ጎማዎች፤ 60 ትላልቅ አሮጌ ጎማዎች፤ 25 ኋይት ቦርድ፤ 31 OK ፕሪንተር፤ 3 ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ 160 ኮምፒዩተር ፤ 65 የኮምፒዩተር እስከሪን፤ 3 የውሃ ማጣሪያዎች፤ 2 ፕሮጀክተሮች፤ 100 እስታብላይዘሮች፤ 40 የመኪና ባትሪዎች፤ 20 ትልቅና ትንሽ የብረት ቁም ሳጥኖች፤ ሳይወገዱ በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ መሆኑ፤
- 4 የዲሽ ሳህኖች፤ በርካታ የተማሪ ወንበሮች እና 580 የቤት ክዳን ቆርቆሮዎች መወገድ ሲገባቸው በዋናው ግቢ ሜዳ ላይ ተጥለው የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

6.2 <u>ስጋት፤</u>

መወገድ የሚገባቸው ዕቃዎች በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ካልተወገዱ የዕቃ ግምጃ ቤቶችን አላግባብ ያጣብባሉ፤ እንዲሁም በመሸጥ ከሚወገዱ ዕቃዎች የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኘት አያስችልም፡፡

6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዲስተካከሉ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

6.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ንብረቶች የአገልግሎት ግዜያቸው ያለቀና ለዩኒቨርሲቲው ዳግመኛ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ በመሆናቸው ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/11/289 በተጻፈልን ደብዳቤ መሠረት ለአወጋገድ በሚያመች መልኩ በዓይነትና ብዛት ተለይተው ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት እንድንልክ በተጠየቅነው መሠረት ከዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና ፋይናንስ ልማት ም/ፕሬዝደንት ጽ/ቤት በቁጥር jju/ advp/153/09 በቀን 22/10/2009 ዓ.ም.፤ በቁጥር jju/ advp/154/09 በቀን 22/10/2009 ዓ.ም. እና እንዲሁም በቁጥር jju/advp/156/09 በቀን 22/10/2009 ዓ.ም. በተጻፉ ደብዳቤዎች መሠረት ንብረቶቹን በህጉ መሠረት ማስወገድ እንዲቻል ለግዥና የንብረት ማስወገድ አገልግሎት ኤጀንሲ የላክን ከመሆኑም ባሻገር በዚሁ መሠረት ከኤጀንሲው የተላኩት ባለሙያዎች የ346 ትናንሽና ትላልቅ አሮጌ የመኪና ጎማዎችን፤ 25 የሚሆኑ የዋይት ቦርድ፤ 31 OK Printer፤ 3 የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ በብዛት 160 የሚሆን ኮምፕዩተር፤ ብዛታቸው 65 የሚሆን Desk Top ኮምፕዩተር እስክሪን፤ 3 የውሃ ማጣሪያ እና ሁለት ፕሮጀክተሮች፤ በቁጥር 100 የሚሆኑ እስታብላይዘር እና 40 የሚሆኑ የመኪና ባትሪዎች፤ 20 የሚሆኑ ትላልቅና ትናንሽ የብረት ቁም ሳጥኖችንና እንዲሁም 16784 ኪ.ግ. የሚመዝኑ ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶችን ለክተው የሄዱ በመሆኑ በቀጣይነት ንብረቶቹን እንዲያነሱልን በመጠባበቅ ላይ ያለን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ 580 ቆርቆሮዎችን በተመለከተ የዩኒቨርሲቲው የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ በሐራጅ እንዲሸጡ በወሰነው መሠረት በሐራጅ ተሸጠው እነዲወገዱ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ነው፡

7. <u>ተሽከርካሪዎች፤</u>

7.1. <u>ግኝት፤ የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል አራት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ከሀ-ሰ ስለመንግስት ተሽከርካሪዎች

የህይወት ታሪክ ምዝገባ በሚለው ስር ‹‹የመንግሥት መ/ቤት በግዥ፣ በስጦታ፣ በዝውውር…ወዘተ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ ቢያንስ የሚከተሉት መረጃዎች መዝግቦ ይይዛል፤ የተሽከርካሪውን አይነትና ሞዴል፣ የጭነቱ ልክ (በሰው፣ በኩንታል፣ በኪዩቢክ ሜትር ወይም በሊትር ተለይቶ)፤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሮች፣ የሚጠቀመው የነዳጅ አይነት፤ የተገዛበት ወይም በመ/ቤቱ ባለቤትነት ሥር የዋለበት ቀንና ዓመተ ምህረት፤ የተሽከርካሪው ዋጋ እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ቁጥር›› መያዝ እንዳለበት መመሪያው ያመለክታል፡፡ በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፤

- ኮድ ኢ.ት 4-12236 ላንድ ኩሩዘር በብልሽት ምክንያት ከ7 ወር በላይ የቆመ ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-12470 ማርቸዲስ በብልሽት ምክንያት 5 ዓመት የቆመ መሆኑ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-14961 ታታ በብልሽት ምክንያት ከ1 ዓመት በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-12315 ሚትስቡሺ ለረጅም ዓመታት በብልሽት ምክንያት የቆመ ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-14962 ታታ በብልሽት ምክንያት ከ9 ወር በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-17441 ማዝዳ ፒክአፕ በግጭት ምክንያት ከ2 ወር በላይ የቆመ ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-20774 ሚኒባስ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌለው መሆኑ፤
- ኮድ ኢ.ት 4-12998 እና ኢ.ት 4-14195 ኒሳን ፒክአፕ መኪናዎች የኪሎ ሜትር ቆጣሪ (ጌጃቸው) የማይሰራ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

7.2 <u>ስጋት፤</u>

- የመንግስት ንብረት ሲበላሽ ወዲያውኑ ጥገና ተደርጎለት አገልግሎት እንዲሰጥ አለማድረግ ለበለጠ ብልሽት የሚዳርግ ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስትን አግባብ ላልሆነ ወጪ የሚዳርግና በተቋሙም አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

- ተሽከርካሪዎችን ያለሰሌዳ ቁጥር መያዝ ከመመሪያ ውጭ ከመሆኑም በተጨማሪ ንብረቱ የተቋሙ መሆኑን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

- የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎችን ለሥራ ማሰማራት የነዳጅ ፍጆታን ለመቆጣጠር ስለማያስችል የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

7.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ ላይ የታዩት የአሠራር ግድፈቶች እንዲስተካከሉ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

7.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

በኮድ ኢ.ት 4- 14962 ታታ (Tata) እና እንዲሁም በኮድ ኢ.ት 4- 12315 ሚትስቢሺ (Mitsubishi) ተሽከርካሪዎች በቁጥር JJU/ADVP/293/2010 በቀን 25/01/2010 በዩኒቨረሲቲው የፋይናንስና አስተዳደር ልማት ም/ፕሬዝደንት ጽ/ቤት ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴርና ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ኤጀንሲ በተጻፈ ደብዳቤ እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች ከአገልግሎት ግዜያቸው አኳያ በየግዜው በሚያጋጥማቸው ተደጋጋሚ ብልሽት የሚጠይቁት የጥገና ወጪና የሚጠቀሙት ነዳጅ ከፍተኛ በመሆኑ በህጉ መሠረት እንዲወገዱ ያስተላለፍን ከመሆኑም ባሻገር ተሽከርካሪዎቹ በግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ኤጀንሲ በኩል በቅርቡ የሚነሱ መሆኑን በመጠባበቅ ላይ ያለን መሆኑን፤ በኮድ ኢ.ት 4- 12236 ላንድ ክሩዘር (Land Cruiser) እና በኮድ ኢ.ት 4- 14961 ታታ (Tata) እንዲሁም በኮድ ኢ.ት 4-12470 ማርቼዲስ(Mercedes Benz) ተሽከርካሪዎች በ2010 የበጀት ዓመት በዩኒቨርሲቲው የተሽከርካሪ ጥገናና እድሳት አገልግሎት ግዥ ጨረታ ወጥቶ እንዲታደሱ በመጠባበቅ ላይ ያለን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በኮድ ኢ.ት 4- 17441 ማዝዳ ፒክ አፕ (Mazda Pickup) ተሽከርካሪን በተመለከተ ለተሽከርካሪው መቆም ምክንያት የሆነው የግጭት አደጋ የተከሰተው ከወር በፊት በመሁኑና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች የመድህን ዋስትና አገልግሎት ሽፋን እንዲሰጥ ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውል ከገባው የዋስትና ሰጪ ድርጅት ጋር በመነጋገር በዩኒቨርሲቲውና በዋስትና ሰጪ ድርጅቱ መካከል ባለው የተሽከርካሪ ዋስትና ውል መሠረት ተገቢውን ጥገና እንዲያገኝ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

8. የክትትል ኦዲት፤

8.1.1. ከ2007 - 2008 በጀት ዓመት የሕጋዊነት ኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች በተመለከተ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምሰት አንቀጽ 17/3 መሠረት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች

በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲው ከ2007 - 2008 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ከዚህ በታች በተገለጹ ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>**በ2007 በጀት ዓመት የተገኘ ግኝት፤**</u>

- ዩኒቨርሲቲውን ለለቀቁ ሠራተኞች አላግባብ የተከፈለው ብር 17,563.86 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

<u>**በ2008 በጀት ዓመት የተገኘ ግኝት፤**</u>

- ዩኒቨርሲቲው በውሉ በተቀመጠው የማስረከቢያ ቀን መሠረት ግንባታውን አጠናቀው ያላስረከቡ 4 የሕንጻ ተቋራጮች የሕንፃ ግንባታውን ላዘገዩበት የጉዳት ካሳ (ቅጣት) ብር 11,482,841.00 እንዲከፍሉ ያላደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

7.1.2 <u>ሥጋት</u>

በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሠረት የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ በኦዲት ወቅት የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዳይታረሙ ከማድረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

7.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በኦዲት ግኝቱ ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1. የ2009 በጀት ዓመት በጀት ማመዛዘኛ

1. ያልተሰራበት በጀት (መደበኛ በጀት)				
	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ያልተሰራበት	መቶኛ
6111	164,577,418.00	138,627,103.47	25,950,314.53	16%
6113	2,001,000.00	1,000.00	2,000,000.00	100%
6114	19,329,000.00	958,560.00	18,370,440.00	95%
6116	16,245,000.00	9,336,816.04	6,908,183.96	43%
6124	2,136,000.00	1,858,196.31	277,803.69	13%
6131	18,371,014.90	14,899,711.17	3,471,303.73	19%
6211	5,531,830.00	2,718,443.25	2,813,386.75	51%
6213	4,357,000.00	3,650,073.94	706,926.06	16%
6214	15,900,000.00	545,738.15	15,354,261.85	97%
6217	6,265,000.00	4,159,044.86	2,105,955.14	34%
6218	3,367,640.00	1,145,882.23	2,221,757.77	66%
6219	3,257,800.00	2,903,580.04	354,219.96	11%
6223	12,000,000.00	2,635,047.74	9,364,952.26	78%
6232	4,357,700.00	2,824,148.15	1,533,551.85	35%
6233	3,376,200.00	2,819,064.72	557,135.28	17%
6243	8,400,130.90	455,864.36	7,944,266.54	95%
6253	575,000.00	194,755.40	380,244.60	66%
6254	1,240,500.00	1,062,648.18	177,851.82	14%
6255	795,000.00	513,990.06	281,009.94	35%
6256	582,000.00	143,316.37	438,683.63	75%
6257	4,200,000.00	1,773,033.68	2,426,966.32	58%
6258	4,700,000.00	1,888,533.32	2,811,466.68	60%
6259	2,600,000.00	1,809,279.19	790,720.81	30%

6271	4,150,000.00	2,154,758.76	1,995,241.24	48%
ድምር	**308,315,233.80**	**199,078,589.39**	**109,236,644.41**	
2. ያልተሰራበት በጀት (ካፒታል በጀት)				
	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ያልተሰራበት	መቶኛ
6313	39,419,000.00	24,089,268.36	15,329,731.64	39%
6314	62,334,869.10	51,599,917.23	10,734,951.87	17%
6315	40,000.00	--.--	40,000.00	100%
6324	74,631,700.00	38,448,541.29	36,183,158.71	48%
ድምር	**176,425,569.10**	**114,137,726.88**	**62,287,842.22**	
3. ያልተሰራበት በጀት (ከውስጥ ገቢ)				
	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ያልተሰራበት	በመቶኛ
6114	10,000.00	9,000.00	1,000.00	10%
6212	123,500.00	55,890.00	67,610.00	55%
6215	200,000.00	131,000.00	69,000.00	35%
6219	238,100.00	180,458.69	57,641.31	24%
6251	15,000.00	9,595.00	5,405.00	36%
6253	30,000.00	24,932.00	5,068.00	17%
6412	291,800.00	217,408.50	74,391.50	25%
ድምር	**908,400.00**	**628,284.19**	**280,115.81**	
ያልተሰራበት በጀት ድምር (የመደበኛ፣ ካፒታልና የውስጥ ገቢ)			171,804,602.44	
በ4251 ለኮንትራክተሮች በቅድሚያ የተከፈለ			(101,271,454.32)	
በ4253 ለአቅራቢዎች በቅድሚያ የተከፈለ			(34,532,135.12)	
የተስተካከለ ያልተሰራበት በጀት ድምር			36,001,013.00	